Week 13

Grade 2

# የጤና ስጋቶች



Leveled

# የጤና ስጋቶች

Leveled | Grade 2 | Week 13



ይህ አጋዥ የንባብ መጽሐፍ ከዩ.ኤስ.ኤ.አይ.ዲ. (USAID) በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ በሴቭ ዘ ቺልድረን (Save the Children)፣ በትምህርት ሚኒስቴር እና በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ የጋራ ትብብር ተዘጋጅቶ ታተመ::

2008 ዓ.ም.

The CC By license lets others distribute, adjust, and build upon this work, for free or commercially, as long as credit is given to the original creation. However, any changes from the original must be indicated.

For more info please refer: *https://creativecommons.org/licenses/*




የጤና ስጋቶች ብዙ ናቸው።



ከጤና ስጋቶች መካከል አንዱ የአካባቢ ንጽህና አለመጠበቅ ነው፡፡



ሰዎች ቤታቸውንና ግቢያቸውን ሊያጸዱ ይችላሉ።



ነገርግን ቆሻሻዎችን በየሚዳውና በየቦታው ይጥላሉ፡፡



በየሜዳው የሚጣሉ ቆሻሻዎች ዝንቦችን ይሰበስባሉ።



መጥፎ ሽታ ያመጣሉ::
ዝንቦችም በምግብ ላይ ያርፋሉ::



በየቱቦው የሚጣሉ ቆሻሻዎች ደግሞ የውኃ መፋሰሻ ቦዮችን ይዘጋሉ።



በየቱቦው ውስጥም ይበሰብሱና በመጥፎ ጠረን አካባቢውን ይበክላሉ።



እነዚህ ብስባሾች በክረምት ወራት ከጎርፍ ጋር ይቀላቀላሉ።



ውኃማ አካላትንና አካባቢን ይበክላሉ፡፡



ሰዎችና እንስሳት የተበከለ ውኃ ይጠጣሉ።



በእነዚህ ምክንያቶች ሰዎች ለተላላፊ በሽታዎች ይጋለጣሉ።